## *ከእስር ቤት የአዲስ ዓመት መልካም ምኞት መግለጫ*

## *ለነፃነትህ እየታገልክ ያለኸው የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ!*

- *ለነፃነትና ዲሞክራሲ በተደረገዉ ትግል ቤተሠባችሁ የተሠዋባችሁ፣*
- *የነፃነት ጮራ እንዲፈነጥቅ በመታገላችሁ በየገጠሩ በተደበቁ እስር ቤቶች ታጉራችሁ በሥቃይ ላይ ለምትገኙ የሠላምና ዲሞክራሲ ጀግኖች፣*
- *በአምባገነኖች የሚደርስባችሁን ወከባ ተቋቁማችሁ፣ በገዛ ቤታችሁና መንደራችሁ መዋያና ማደሪያ አጥታችሁ፣ ለሠላምና ለነፃነት ቀን መዳረስ መስዋዕት እየከፈላችሁ ላላችሁ ሁሉ፣*
- *አሁንም በየአካባቢው ትግሉን እያቀጣጠላችሁ የሀገር ተስፋ ለሆናችሁ ወጣቶች፣*
- *በአገራችሁ እንዳትኖሩ በመደረጉ በመላ ዓለም ተበትናችሁ በስደት የምትኖሩ አገር ወዳዶች በሙሉ፣*

*ነፃነትና ዲሞክራሲን እውን ለማድረግ ለብዙ ዓመታት መስዋዕትነት ስትከፍሉ ቆይታችኋል:: ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም የምትፈልጉትን አመራር መርጣችኋል፣ በዚሁ ዕለትም የዛሬው ገዢ ቡድንን እንደማትፈልጉ በማያወላውል ሁኔታ ድምፅ ሰጥታችሁ አሳውቃችኋል::*

*ነገር ግን አምባገነኖች ሽንፈትን በወቅቱ ለመቀበል ተፈጥሮዓቸው ስለማይፈቅድላቸዉ የህዝብን ድምፅ ረጋገጡ:: በዚህም የተነሣ ብዙ የዲሞክራሲ ታጋዮች ተገደሉ፣ ታሠሩ::*

*የሥልጣን ስግብግብነታቸው የፈጠረዉ ጉልበት በሥልጣን ላይ የሚያቆይ ቢመስላቸውም የህዝቡን የዲሞክራሲና የነፃነት ጉጉት አፈረጠሙት እንጂ እንደ ፍላጎታቸው ትግሉን ሊያዳፍኑት አልቻሉም:: እንዲያዉም መላዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከቀድሞ በበለጠ ተባብሮ በአንድነት እንዲታገል አድርገውታል:: ኢትዮጵያዉያን ድርጅቶችም ዛሬ ከትናንቱ በበለጠ ለሀገር የጋራ ጥቅም ተባብረዋል:: ስለዚህም የነፃነት ቀን እየተቃረበ ነው::*

*በቅንጅት ዙሪያም ተሠብስባችሁ ታግላችኋል:: እኛም እናንተን አምነን የነፃነቱን ትግል ለማጠናከር ተሠልፈናል:: ለዚህ የተከበረ የህዝብ ዓላማ ብንታሠርና ሰብዓዊ መብቶቻችን ተደፍረዉ ብንጉላላም ለህዝቡ ያለንን ወገናዊነት ይበልጥ ተረጋገጠ እንጂ በእኛ በኩል አንዳችም የማፈግፈግ አዝማሚያ እንደሌለ እናረጋግጥላችኋለን:: ነፃነትና ዲሞክራሲ የሚገኘው በከፍተኛ መስዋእትነት ስለሆነ በአካል ከእናንተ ብንለይም በልብ ከእናንተው ጋር ነን::*

*የ1998 ዓ.ም የትግል ዓመት ተገባዶ አዲሱ አጭር የትግል ወቅት ቀርቧል:: 1999 ዓ.ም የነፃነት መጎናፀፊያ ዓመት እንዲሆን እንመኛለን::*

*ኢህአዴግ የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነትና ዲሞክራሲን አያዉቅም ብሎ ገምቶ የነበረ ቢሆንም ሕዝባችን የዲሞክራሲ እውቀቱና የነፃነት ጥማቱ በግንቦት 97 ምርጫ በጉልህ አሣይቷል:: በዚህም የአምባገነኖች ጭንብል ወልቋል:: ይሁን እንጂ የዉጭዉ ዓለም ነፃነትን ያጎናፅፈናል ብለህ አታስብ::*

*ነፃነትና ዲሞክራሲ እውን የሚሆነው በእናንተና በእኛ የተባበረ ጥረት ብቻ መሆኑን አውቃችሁ የትግላችሁን ደረጃ ከፍ ማድረግ ይጠበቅባችኋል። ያዝ ለቀቅ ሳይሆን ያለማሰለስ ከቀን ወደ ቀን የጠነከረ ግፊት ማካሄድ - ከባድ ቢሆንም - እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ልናስገነዝባችሁ እንወዳለን።*

*የእኛ መታሠር ትግሉን አጠናከረ እንጂ አላበረደውም። ይህ ለአምባገነኖች ትልቅ ውድቀት ነዉ። በዘርና በሀይማኖት ሊለያዩን ያጠመዱትን ወጥመድ ማምከናችሁ ትልቅ እመርታ ነውና ትደነቃላችሁ።*

*በውጭ አገሮች ያላችሁም የአገር አለኝታዎች እስከ አሁን ላደረጋችሁት ትግል እያመሰገንን ለወደፊቱም አጠናክራችሁ እንደምትገፉበት እርግጠኞች ነን።*

*በመጨረሻም በጎርፍ አደጋ ጉዳት ለደረሰባቸዉ ቤተሰቦች የተሰማንን ጥልቅ ሐዘን እንገልፃለን።*

*መጪዉ ዓመት ኢትዮጵያ ከአምባገነን አመራር ነፃ የምትወጣበት ዓመት እንዲሆን እንመኛለን። መልካም አዲስ ዓመት።*

*የሕዝብ አሸናፊነት ይረጋገጣል!!*

***በኢትዮጵያ እስር ቤቶች የታሰሩ የቅንጅት አመራር አባላትና ታጋዮች***
***ነሐሴ 30 ቀን 1998 ዓ.ም***
***አዲስ አበባ***